## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### እኔ ለማመልከት ብቁ ነኝ?

ለማመልከት ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን ሁለት ዋና ዋና የብቁነት መስፈርቶች የግድ ማሟላት ይኖርብዎታል፦

1) ማመልከቻዎችን ለመቀበል ጥሪ የተላለፈበት ሀገር ዜጋ ወይም ቋሚ ነዋሪ መሆን። ጥሪው የተላለፈበት ሀገር ዜጋ ሆነው የሚኖሩት ግን ውጭ ሀገር ከሆነ ለማመልከት ብቁ እንደማይሆኑ ስንገልጽ ሀዘን እየተሰማን ነው።

2) የፊልም ሰሪነት ታሪክ ያለዎት መሆን። ይህም ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ወይም በሀገር ውስጥ ቢያንስ አንድ ሥራ (ለምሳሌ ወጥቶ የታየ ቴአትር፤ በብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ፌስቲቫል ላይ የታየ፣ በቴሌቪዥን የተላለፈ፣ በዲጂታል መንገድ በሦስተኛ ወገን የተላለፈ፣ ስትሪም/stream የተደረገ ወይም እንደፍላጎት እንዲታይ/በVOD የቀረበ ሥራ) ያወጡ መሆን አለብዎት የሚል መስፈርት አለን ማለት ነው። ይህም አጭር ፊልምንም ይጨምራል።

### በአንድ ፊልም ሥራ ውስጥ የማዳበር ምዕራፍ ማለት ምን ማለት ነው? ማመልከት የምችለው በትክክል ምን ለማግኘት ነው?

አንድ ፊልም ከመሰራቱ በፊት “የማዳበር ምዕራፍ” ውስጥ ማለፍ ይኖርበታል። ይህ ምዕራፍ በማንኛውም ፊልም ዝግጅት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ሲሆን የፊልሙን ሀሳብ ማዳበርን/ግልጽ ማድረግን፣ የፊልሙን አጽህሮተ ታሪክ (treatment) እና የፊልም ጽሁፍ (screenplay) መጻፍን፣ ፋይናንስ ማግኘትን፣ ከፊልሙ ጋር የተያያዙ መብቶችን በተመለከተ መዋዋልን፣ ወዘተ ያካትታል።

ከዶቸ ቬሌ አካዳሚ የፊልም ልማት ፈንድ (DW Akademie Film Development Fund) የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ከሚችሉ የማዳበር እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል (በዚያ ግን የተወሰነ አይደለም)፦ በፊልምዎ አጽህሮተ ታሪክ እና የፊልም ጽሁፍ ላይ የሚሰራ ሥራ፣ ጥናት (ጉዞ)፣ ከሌሎች ፊልሞች የተወጣጣ ፕሮቫ (mood reel) ወይም ፕሮቫ ማዘጋጀት፣ በፊልም ስልጠናዎች (film labs) ላይ መሳተፍ (የስልጠና ክፍያ)፣ ለፊልሙ ዝግጅት ፋይናንስ ማፈላለግ (ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎችን የማቅረብ ሥራ)፣ ወደ ፌስቲቫሎች መጓዝ፣ የቀረጻ ስፍራ ማፈላለግ ወይም ተዋንያን መመልመል፣ ወዘተ።

የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት ከሚችሉባቸው ፊልምን የማዳበር ወጪዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ የጥናት ወጪዎች
- የድርሰት አርታኢ ወጪዎች
- የደራሲ ወጪዎች
- ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ የጉዞ ወጪዎች
- የስልጠና፣ የኮንፈረንስ፣ የገበያ ወጪዎች
- ከሌሎች ፊልሞች የተወጣጣ ፕሮቫ (mood reel) ለማዘጋጀት የሚወጡ ወጪዎች
- ጠቅላላ ወጪዎች (ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ የስልክ፣ የቢሮ ኪራይ፣ ወዘተ)
- ከፊልሙ ጋር የተያያዙ መብቶችን ለማግኘት የሚወጡ ወጪዎች
- የሕግ ምክር አገልግሎት

## ምን ምን ሰነዶችን ማስገባት ይኖርብኛል?

- የማመልከቻ ቅጽ (ኢንተርኔት ላይ)
- የታሰበው ፕሮጀክት አጭር ገለጻ (ቢበዛ 2 ገጽ)
- የተግባራት ሰንጠረዥ፡- በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ዕውን እንዲሆኑ የተቀመጡት ውጤቶች ላይ ለመድረስ እንዲከናወኑ የታቀዱት ተግባራት ዝርዝር እና የጊዜ ሰሌዳ
- በገንዘብ ድጋፉ (10.000 ዩሮ) ሊያከናውኗቸው ላሰቧቸው የፊልም ማዳበር እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልገው በጀት

**ፕሮጀክታቸው የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለፈላቸው አመልካቾች አጽህሮተ ታሪክ (ቢበዛ 8 ገጽ) እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ**

ፕሮጀክትዎ የመጀመሪያውን ማጣሪያ ያለፈ እንደሆነ ዶቸ ቬሌ አካዳሚ ያሳውቅዎታል። ይህም የማመልከቻ ጊዜው ካበቃ ከአራት ሰምንታት በኋላ የሚከናወን ይሆናል።

## በጀቱ ውስጥ ምን ምን ወጪዎችን ማካተት እችላለሁ?

በፕሮግራሙ ውስጥ ለማከናወን ላቀዷቸው ፊልምን የማዳበር እንቅስቃሴዎች ለማውጣት ያቀዷቸውን ወጪዎች በሙሉ ማካተት ይችላሉ። ከእነዚህ ወጪዎች ውስጥም የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የጽሁፍ
- የጥናት ወጪዎች
- የሠራተኛ ወጪዎች (የድርሰት አርታኢ ክፍያዎች፣ የደራሲ ክፍያዎች፣ የሂሳብ ባለሙያ ክፍያዎች፣ ወዘተ)
- የጉዞ ወጪዎች
- የስልጠና፣ የኮንፈረንስ፣ የገበያ ወጪዎች
- የፊልም ካታሎግ (lookbook) ወይም ከሌሎች ፊልሞች የተወጣጣ ፕሮቫ (mood reel) ለማዘጋጀት የሚወጡ ወጪዎች
- የቢሮ ኪራይ
- ከፊልሙ ጋር የተያያዙ መብቶችን ከማግኘት የሚወጡ ወጪዎች
- የህግ ምክር አገልግሎት
- …

## የተወሰነውን የዓመቱን ክፍል የማሳልፈው በቋሚነት ከምኖርበት ሀገር ውጭ ነው። እንደዚያም ቢሆን ለማመልከት ብቁ ነኝ?

ውጭ ሀገር የሚኖሩ ፊልም ሰሪዎች ማመልከት እንደማይፈቀድላቸው ስንገልጽ ሀዘን እየተሰማን ነው። ማመልከት የሚችሉት ማመልከቻዎችን ለመቀበል ጥሪ በተላለፈበት ሀገር ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ እና የሚሰሩ አመልካቾች ብቻ ናቸው።

## በማመለክትበት ወቅት መጠቀም ያለብኝ ቋንቋ ምንድን ነው?

በእንግሊዝኛ እንዲያመለክቱ እንጠይቃለን። በሌላ ቋንቋ የተዘጋጁ ሰነዶችን ከማመልከቻዎ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡ ከሆነ እባክዎ የእንግሊዝኛ ትርጉማቸውንም ያካትቱ።

## በማመልከቻዬ ውስጥ የሚያስፈልጉኝን ስልጠናዎች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ ያለብኝ ለምንድን ነው?

በልክዎ የተዘጋጀ እና ለእርስዎ ተለይቶ የተዘጋጀ የስልጠና ፕሮግራም ማቅረብ እንድንችል የትኞቹ የስራ ዘርፎች ላይ ስልጠና ቢያገኙ ፕሮጀክትዎን በላቀ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ እና የሙያ ክህሎቶችዎን ለማሻሻል እንደሚረዳዎት ለማወቅ የሚያስችል ዝርዝር መረጃ ያስፈልገናል።

## ከማመልከቴ በፊት ከዶች ቬሌ አካዳሚ ጋር የሚደረግ የምክክር ስብሰባ ላይ መገኘት ይኖርብኛል?

አያስፈልግዎትም፤ ዶች ቬሌን ማማከር ግዴታ አይደለም። ነገር ግን ማመልከቻዎችን ለመቀበል ጥሪ ከተላለፈ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በኢንተርኔት አማካኝነት የሚደረገው የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜ ላይ እንዲገኙ አጥብቀን እንመክራለን። ስብሰባው ማመልከቻ የሚቀርብበትን ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎታል እንዲሁም ጥያቄዎችን በቀጥታ ለዶች ቬሌ አካዳሚ ለማቅረብ ያስችልዎታል። የስብሰባው ቀን ድረ ገጻችን ላይ የሚገለጽ ይሆናል።

## የፊልሜን ሀሳብ የሚገልጸው አጭር ጽሁፍ ምን ምን ያካተተ መሆን አለበት?

በአጭር ጽሁፉ ውስጥ የፊልምዎን ታሪክ በአሁን የጊዜ ሰዋሰው ግልጽ እና አጭር በሆነ ቋንቋ መግለጽ ይኖርብዎታል፡-ፊልምዎ የሚያሳየው ነገር ምንድን ነው? የፊልምዎ ማዕከላዊ ታሪክ ምንድን ነው?

የፊልሙን ዋና ገጸ ባህሪያት፣ የታሪኩን መነሻ ሀሳብ እንዲሁም ግጭቱን መግለጽ ይኖርብዎታል፡- የፊልሙ ገጸ ባህሪያት/ዋና ገጸ ባህሪ ማሳካት የሚፈልጉት ነገር ምንድን ነው? የፊልሙ ገጸ ባህሪያት/ዋና ገጸ ባህሪ ግባቸው ምንድን ነው?

**ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ጽሁፍ እንዲያቀርቡ በትህትና እንጠይቃለን።**

## የፊልም ገላጭ አረፍተ ነገር (logline) ምሳሌዎች አሏችሁ?

ያስተውሉ፡- እነዚህ ለማጣቀሻ ብቻ የቀረቡ የፊልም ገላጭ አረፍተ ነገር ምሳሌዎች ናቸው። አንድ ፊልም ገላጭ አረፍተ ነገር ሊጻፍ የሚችልበትን መንገድ እንዲያሳዩ ታስበው የቀረቡ ናቸው። እነዚህ የፊልም ገላጭ አረፍተ ነገር ምሳሌዎች አመልካቾች ለሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶች ይዘት እንደ ግብአት እንዲያገለግሉ ታስበው የቀረቡ በፍጹም እንዳልሆኑ በአጽንኦት ለመግለጽ እንወዳለን።

- “ከአንድ ድንቅ ከሆነ የባንክ ዘረፋ በኋላ ዘረፋውን የፈጸሙት ሌቦች ከመካከላቸው ለፖሊስ መረጃ የሚያቀብል ሰው እንዳለ ይጠረጥራሉ።”
- “በቤተሰቦቿ ያዘነች አንዲት ወጣት ሴት የገጠር ህይወቷን ጥላ ወደ ትልቅ ከተማ ትሄዳለች። በዚያ ሳለች ግን የማንነቷ እውነተኛ መነሻ የት እንደሆነ ትደርስበታለች።”
- “በጣም የተለያዩ የሙያ ህልሞች ያሏቸው ሁለት የትምህርት ቤት ጓደኛሞች በህይወታቸው ውስጥ ወሳኝ አጋጣሚዎች ላይ ደግመው ደጋግመው ይገናኛሉ፤ በመጨረሻም እንደሚዋደዱ ይገለጽላቸዋል።”
- “ከተለያየ የጀርባ ታሪክ በመጡ ሦስት እንስት ዋና ገጸ ባህሪያት ላይ በማተኮር በሴቶች ላይ ወደሚፈጸም ጥቃት የሚያመሩ ማህበራዊ መዋቅሮችን የሚያጋልጥ ዘጋቢ ፊልም ነው።”
- “አንድ የ16 ዓመት ልጅ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቤተሰቦቹን ለመርዳት ሲል ስኬታማ እግር ኳስ ተጫዋች የመሆን ህልሙን ለመተው ይወስናል – ከዚያ ግን ድንቅ የእግር ኳስ ተሰጥኦውን የሚያሳይበትን ዕድል ያገኛል።”

## አጽህሮተ ታሪክ ምንድን ነው?

አጽህሮተ ታሪክ የሚጻፈው የፊልም ጽሁፉ ከመጻፉ በፊት ነው። የፊልሙ ታሪክ አጭር ትረካ ነው። አጽህሮተ ታሪክ ከፊልም ጽሁፍ ያጥራል እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ ዝርዝር ንግግር አይኖረውም። አጻጻፉ በአሁን የጊዜ ሰዋሰው እንደተጻፈ አጭር ታሪክ መሆን አለበት። በአጽህሮተ ታሪክዎ ውስጥ ዋናውን ገጸ ባህሪ እና ለማድረግ የሚፈልገውን ነገር በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም ገጸ ባህሪዎ በታሪኩ ውስጥ የሚያልፍበትን የለውጥ እና የዕድገት ሂደት መግለጽ ይኖርብዎታል። በአጽህሮተ ታሪክዎ ውስጥ የገጸ ባህሪውን ዕድገት እና የፊልምዎን ታሪክ አስረግጠው የሚያሳዩ የተመረጡ ትዕይንቶችን ማካተት ይችላሉ።

**የዘጋቢ ፊልም** አጽህሮተ ታሪክም እንዲሁ የፊልሙን ዋና ገጸ ባህሪ እና በፊልምዎ ውስጥ መከተል የሚፈልጉትን የዋና ገጸ ባህሪውን "ጉዞ" እንዲሁም ሊያተኩሩበት(ባቸው) የሚፈልጉትን ችግር(ሮች) የሚጠቁም መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም የዘጋቢ ፊልምዎ አጽህሮተ ታሪክ የምስል አቀራረብዎንም ያንጸባርቃል። ለምሳሌ የፊልሙ ሰሪ የሆኑት እርስዎ በፊልሙ ላይ ድምጽዎ የሚሰማ ወይም የሚታዩ እንደሆነ ሊገልጹ ይችላሉ። የፊልምዎን ዋና ገጸ ባህሪ አግኝትው ያናገሩት ወይም ደግሞ (የሙከራ) ቀረጻዎችንም ጭምር ያከናወኑ ከሆነ በአጽህሮተ ታሪክዎ ውስጥ እነዚህን ትእይንቶች ማብራራት ይችላሉ። ቀረጻውን ለማከናወን ገና ዕድሉን ያላገኙ ከሆነ ያከናወኑትን ጥናት መሰረት በማድረግ የፊልምዎን አጠቃላይ ገጽታ እና ስሜት መግለጽ ይችላሉ።

**ፕሮጀክትዎ በቅድመ መረጣ ከተመረጠ ቢበዛ 8 ገጽ የሆነ አጽህሮተ ታሪክ ማቅረብ ይኖርብዎታል። እባክዎ አጽህሮተ ታሪኩን በእንግሊዝኛ ይሙሉ።**

## ፕሮግራሙ ለምንድን ነው የሙያ ድጋፍ (fellowship) ፕሮግራም ተብሎ የሚጠራው? ፕሮግራሙ ምን ምንን ያካትታል?

ለአንድ አመት የሚቆይ የሙያ ድጋፍ ውል ይፈርማሉ። ፕሮግራሙ የ10,000 ዩሮ የገንዘብ ድጋፍን፣ ለአንድ አመት የሚቆይ የአንድ ለአንድ የስልጠና (mentorship) ፕሮግራምን እንዲሁም ተጨማሪ የስልጠና እና የትውውቅ ክፍለ ጊዜዎችን ያካትታል።

## የገንዘብ ድጋፉ የሚሰጠኝ በምን መልኩ ነው?

የገንዘብ ድጋፉ እያንዳንዳቸው 2,500 ዩሮ በሆኑ አራት ክፍያዎች የሚሰጥ ይሆናል። የመጀመሪያው ክፍያ ውል ከተፈረመ በኋላ ይፈጸማል። ቀጣዩ ክፍያ ከመተላለፉ በፊት የተራመዱትን እርምጃ የሚያሳዩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። የፕሮጀክት ጊዜው መጨረሻ ላይም የመጨረሻ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የምንጠይቆት ይሆናል።

## የገንዘብ ድጋፉ ለምን ያህል ጊዜ የሚቆይ ነው? የሚጀምረውስ መቼ ነው?

የገንዘብ ድጋፉ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ነው፤ የሚጀምረውም መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም. ነው።

## በገንዘብ ድጋፉ ወቅት ለአንድ ዓመት በሚቆዩ ሌሎች የሙያ ድጋፍ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ እችላለሁ?

የአንድ ለአንድ አሰልጣኝ የሚያገኙበት ሌላ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የሙያ ድጋፍ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ አይቻልም። ነገር ግን የፊልም ስልጠናዎች እና በተግባር እየሰሩ የሚሰጡ ስልጠናዎች (residencies) ላይ መገኘት ይቻላል። መሳተፍ ስለሚችሉባቸው ነገሮች የፕሮግራሙ መጀመሪያ ላይ ከአንድ ለአንድ አሰልጣኝዎ ጋር

እንዲወያዩ እንመክራለን። በአንድ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ እንደሚችሉ ወይም እንደማይችሉ እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎ dw-akademie.film-fund@dw.com ላይ ያነጋግሩን።

## የብቃት ማጎልበቻ ፕሮግራሙ ምን ምንን ያካትታል?

የተመረጡ እንደሆነ ፕሮጀክትዎን በማዳበር ሂደት ውስጥ አመራር የሚሰጥዎት ዓለም አቀፍ የአንድ ለአንድ አሰልጣኝ ይመደብልዎታል።

በተጨማሪም ዶቸ ቬሌ አካዳሚ በተለያዩ ቅርጸቶች እና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለእርስዎ ተስማሚ በሆነ መልኩ የተዘጋጁ የስልጠና እና የትውውቅ መድረኮችን ያመቻችልዎታል። በሚኖሩበት ሀገር በአካል የሚከናወኑ 2-3 የስልጠና ክፍለ ጊዜዎችም ይኖራሉ።

በተጨማሪም ዶቸ ቬሌ አካዳሚ በኢንተርኔት የሚከናወኑ ክፍለ ጊዜዎች እና የትውውቅ ዝግጅቶች ላይ እንዲገኙ ሊጋብዝዎት ይችላል። የገንዘብ ድጋፍ ጊዜው መጀመሪያ ላይ ለቀጣዮቹ 12 ወራት በታቀዱት የስልጠና እና የትውውቅ ዕድሎች ዙሪያ አጭር ገለጻ ይሰጥዎታል።

## ማመልከቻዬ እንደደረሳችሁ ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?

ማመልከቻዎ እንደደረሰን እና ያስገቡት ማመልከቻ የተሟላ መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ ይላክልዎታል። እባክዎ ማልከቻዎ የደረሰን መሆኑን ለማረጋገጥ ቢሮአችንን አያነጋሩ።

## ፕሮጀክቴ የመጀመሪያውን ማጣሪያ እንዳለፈ የማውቅበት መንገድ ይኖራል?

አዎን፣ ፕሮጀክትዎ የመጀመሪያውን ማጣሪያ ካለፈ እናሳውቅዎታለን።

## እንደተመረጥኩኝ የማውቀው መቼ ነው?

የዳኞች ጉባዔው የእርስዎን ፕሮጀክት የመረጠ እንደሆነ በኢሜይል እናሳውቅዎታለን፤ ይህንን የምናሳውቅዎትም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ይሆናል። ይህ የሚሆነው የማመልከቻ ጊዜው ካበቃ ከሁለት ወራት በኋላ አካባቢ መሆኑን በትህትና እንገልጻለን።